# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## በESL ፕሮግራማችን ማን ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል?

- እንግሊዝኛ የማይናገሩ ወይም በቤታቸው ውስጥ ከእንግሊዝኛ ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ አዋቂዎችና የቤተሰብ አባሎች
- በኮሌጅ ኮርሶች ስኬታማ ለመሆን የበለጠ የላቀ የእንግሊዝኛ ችሎታ የሚያስፈልጋቸው ዓለም አቀፍ ተማሪዎች
- የእንግሊዝኛ ችሎታቸውን ማሻሻል ወይም ስለ አሜሪካ ባህል የተሻለ ግንዛቤ ማዳበር የሚፈልጉ በዩ ኤስ ውስጥ የሚገኙ ጊዜያዊና ቋሚ ሠራተኞች

## የESL ትምህርቶች መቼ ይሰጣሉ?

ትምህርቶች የሚቀርቡት በፎል (በልግ)፥ በስፕሪንግ (ጸደይ) እና በሳመር (በጋ) የትምህርት ጊዜ ነው። እንደ ትምህርት ግቢው ቦታ፥ ትምህርቶችን ቀን፥ ማታ ወይም ቅዳሜና እሁድ መከታተል ይችላሉ። ከጊዜ ሠሌዳዎ ጋር የሚስማማ የትምህርት ግቢና ክፍል እንዲያገኙ ልንረዳዎት እንችላለን።

## ምን ዓይነት ኮርሶች አሉ?

ለኮሌጅ ክሬዲት የሚሆኑ ወይም ለክሬዲት ያልሆኑ ትምህርቶችን በአካል ወይም በኢንተርኔት መውሰድ ይችላሉ። ለኮሌጅ ክሬዲት ኮርስ ሲወስዱ፥ በክፍል ሥራዎና በፈተና ውጤቶችዎ መሠረት ለኮርሱ ነጥብ ያገኛሉ። ኮርሱ የኮሌጅ ዲግሪ፥ ዲፕሎማ ወይም ምስክር ወረቀት ለማግኘት ከሚያስፈልጉ በርካታ ኮርሶች ውስጥ አንዱ ነው።

የክሬዲት ያልሆኑ ኮርሶች ዲግሪ፥ ዲፕሎማ ወይም ምስክር ወረቀት ወደማግኘት አያመሩም። ተማሪዎች በተለያዩ የግል ምክንያቶች የክሬዲት ያልሆኑ ኮርሶች ይወስዳሉ።

## ስንት ኮርሶች መውሰድ እችላለሁ?

መውሰድ የሚችሏቸው የኮርሶች ብዛት እንደ እንግሊዝኛ ችሎታዎ፥ በክፍል ውስጥ ለመገኘት የሚችሉበት ጊዜ እና እንደ ዓላማዎ ይለያያል። ትክክለኛውን የሕይወትና ሥራ ሚዛን ለማግኘት አማካሪዎ ከእርስዎ ጋር በቅርበት ይሠራል/ትሠራለች።

## ክፍሎች ምን ያክል ያስከፍላሉ?

ክፍያው ብዙውን ጊዜ በየዓመቱ ይቀያየራል። ክፍያው በእርስዎ የኗሪነት ሁኔታ (በቴኔሲ ወይም ከስቴት ውጪ) እና በሚወስዷቸው የትምህርት ክፍሎች ብዛት ይወሰናል። ስለ ወቅታዊ ክፍያዎች ለማወቅ የኮሌጅዎን ድህረገጽ ይጎብኙ።

## ለESL ክፍሎች ለመክፈል የፌዴራል የገንዘብ ድጋፍ አለ?

ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች ለESL ክፍሎች የገንዘብ ድጋፍ አለ።

## የቀረቡ ፕሮግራሞች

የላቁ ቴክኖሎጂዎች

ንግድ

ትምህርት

እንግሊዝኛ እና ስነ ጥበብ

ሕክምና

ማህበራዊ ሳይንሶች

S.T.E.M.

በአሁኑ ጊዜ የESL ትምህርቶች በሚከተሉት የናሽቪል ስቴት ቦታዎች ይሰጣሉ።

## ደቡብ ምስራቅ ካምፓስ

(በአንቲዮክ ውስጥ)

5248 Hickory Hollow Parkway
Antioch, TN 37013

**NSCC.edu/ESL**

**ESOL@nscc.edu**

የናሽቪል ስቴት ኮምዩኒቲ ኮሌጅ የAA/EEO ቀጣሪ ሲሆን በፕሮግራሞቹና እንቅስቃሴዎቹ ውስጥ በዘር፥ ቀለም፥ ብሔራዊ አመጣጥ፥ ጾታ፥ የአካል ብቃት ወይም ዕድሜ ላይ የተመሠረተ አድሎ አያደርግም። ሕትመት 2019/10/2060

# እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ፕሮግራም



Nashville State Community College



## ወደ ናሽቪል ስቴት ኮምዩኒቲ ኮሌጅ እንኳን ደህና መጡ

የእንግሊዝኛ ቋንቋ የመናገር፥ የማንበብ፥ የመጻፍ እና የመረዳት ችሎታዎን ያሻሽሉ።

የሰለጠኑ አማካሪዎቻችን፥ አስተባባሪዎቻችን እና አስተማሪዎቻችን በናሽቪል ስቴት ኮምዩኒቲ ኮሌጅ የሚሰጠውን የ English as a Second Language (ESL) (እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ፕሮግራም) እንዲረዱ ይረዱዎታል። ለጥያቄዎችዎ መልስ ይሰጣሉ፥ የማመልከቻ ሂደቱን ያስረዳሉ እንዲሁም የግል ግቦችዎን ለማሳካት ዕቅድ ያጎለብታሉ።

**የESL ተማሪዎች የሚከተሉትን የካምፓስ አገልግሎቶች ማግኘት ይችላሉ፦**

- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታዎንና አስፈላጊውን የድጋፍ ደረጃ ለመገምገም የሚሆኑ የፈተና አገልግሎቶች
- ክፍሎች ከመጀመራቸው በፊት የእንኳን ደህና መጣችሁ ክፍለ ጊዜ
- ስኬታማ እንዲሆኑ የሚረዱዎት ትምህርታዊ የምክር ክፍለ ጊዜዎች
- በቤትዎ መሣሪያ ወይም ኢንተርኔት በማይገኝበት ጊዜ ለኮርስ ሥራ የሚሆኑ የኮምፕዩተር ላቦች
- የቤተ መጻሕፍት እና የጥናት ግልጋሎቶች
- አንድ ለአንድ የሚደረጉ የአስጠኚ አገልግሎቶች
- የመማር ችሎታዎ ላይ ተጽዕኖ ለሚፈጥሩ ብቃት ላላቸው የአካል/አእምሮ ጉዳቶች አገልግሎቶች እና ልዩ ማመቻቸቶች
- የእንግሊዝኛ ችሎታዎን መለማመጃ ዕድሎች
- የባለቤትነት ስሜትና ተቀባይነትን የሚሰጡ የተማሪ ክበቦች፥ ድርጅቶች፥ ዝግጅቶች እና እንቅስቃሴዎች

## ወደ ESL ፕሮግራም ለመግባት ማመልከቻ

**እነዚህን ደረጃዎች ይከተሉ**

1. የተሟላ ማመልከቻ ያስገቡ።
2. ተጨማሪ የተማሪ ቅጾች ያስገቡ ኮሌጅዎ በጠየቀው መሠረት። (ሰነድ የሌላቸው ተማሪዎች የስቴት ውጪ ዋጋ ይከፍላሉ)።
3. ከዚህ በፊት ከሄዱባቸው ትምህርት ቤቶች እና ኮሌጆች ኦፊሲዬላዊ የመዝገብ ቅጂዎች (ትራንስክሪፕቶች) ይጠይቁ። ኦፊሲዬላዊ የትምህርት መዝገቦች በATA በተረጋገጠ ተርጓሚ ወደ እንግሊዝኛ መተርጎም አለባቸው።
4. ለኮርስ ምደባ አስፈላጊዎቹን ፈተናዎች ይውሰዱ።
5. ለFree Application for Federal Student Aid (FAFSA) (ለፌዴራል የተማሪ እርዳታ (FAFSA) ነፃ ማመልከቻ) በማስገባት የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት በኢንተርኔት ላይ ያመልክቱ።

የESLፕሮግራምንና ካምፓሳችንን ለማየት ምርጡ መንገድ መጎብኘት ነው! በማንኛውም ጊዜ ካምፓሱን ለመጎብኘት ቀጠሮ ይያዙ።

---

የESL ፕሮግራም የማመልከቻ ሂደት ጊዜ ይፈጃል። ወረቀቶችዎን ለማስገባት ከዚህ በታች ያለውን ሠንጠረዥ እንደ መመሪያ ይጠቀሙ።

| ለመከታተል ያሰቡት የትምህርት ጊዜ | የኮሌጅ ማመልከቻ ያስገቡ | ለገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ያስገቡ |
|---|---|---|
| ፎል ተርም (በኦገስት ወር ይጀመራል) | ሜይ 1 | ሜይ 1 |
| ስፕሪንግ ተርም (በጃኑዋሪ ወር ይጀመራል) | ኦክቶበር 1 | ኦክቶበር 1 |
| ሳመር ተርም (በሜይ ይጀመራል) | ማርች 1 | ማርች 1 |

## ወደ ESL ፕሮግራም ለመግባት ማመልከቻ

**እነዚህን ደረጃዎች ይከተሉ**




በማንኛውም ጊዜ የካምፓስ ጉብኝት ቀጠሮ ይያዙ።